*መመሪያ ቁጥር 562/2013*

*የፍልሰት ተጎጅዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ*

ተጎጂዎችን ስለማዳን፣ ስለመመለስ፣ መልሶ ስለማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበትና ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት ሁኔታ ያለው አሰራር ግልጽነት የሚጎድለው፣ ሰፊ ክፍተት ያለበት እና ቅንጅታዊ አሰራርን ያልተከተለ በመሆኑ፤

ተጎጂዎችን በማዳን፣ በመመለስ፣ መልሶ በማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ በማድረግና ከህብረተሰቡ ጋር በማቀላቀል ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን እና የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ መለየት እና ዝርዝር አሰራራቸውን መወሰን በማስፈለጉ፤

ተጎጂዎችን በማዳን፣ በመመለስ፣ መልሶ በማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት፣ ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት ሁኔታ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ በባለድርሻ አካላት መካከል የሚኖረውን የተጎጅዎች የቅብብሎሽ ሥርዓት እና የቅብብሎሽ ሥርዓቱ የሚሸፍናቸውን ጉዳዮች በዝርዝር መወሰን በማስፈለጉ፤

ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሰዎች የመነገድ እና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 34 (2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍልአንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭርርዕስ**

**ይህ መመሪያ "የፍልሰት ተጎጂዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 562/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡**

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

(1) "አዋጅ" ማለት በሰዎች የመነገድ እና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ነው፡፡

(2) "ተጎጂ ወይም የፍልሰት ተጎጂ" ማለት በአዋጁ ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የተፈጸመበት እና አካላዊ፣ ስነልቦናዊ

ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ወይም እነዚህ ጉዳቶች የደረሱበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ባይሆንም ለወንጀሉ የተጋለጠ ወይም ሊጋለጥ የሚችል በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተመለከተው ጥበቃ እና ድጋፍ እንደ አግባብነቱ የሚያስፈልገው ሰው ነው፤

(3) “ፍልሰት” ማለት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ የሰው ወይም የሰዎች እንቅስቃሴ ሲሆን ስደተኞችን፣የተፈናቀሉ ሰዎችን፣ የኢኮኖሚ ፍልሰተኞችን እና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡

(4) “ፖሊስ” ማለት የክልል ወይም የፌዴራል ፖሊስ ነው፡፡

(5) በአዋጅ ቁ. 1178/12 አንቀጽ 2 እና በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በወጡ ሌሎች አዋጆች እና ደንቦች የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

(6) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነትወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሚከተሉት አካላት እና ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

(1) በአዋጁ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎችመሰረት ወይም በሌላ አግባብ ተጎጂዎችን የማዳን፣የመመለስ፣ መልሶ የማቋቋም፣ ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀል እና ልዩ ልዩ ድጋፍ የማድረግ ተግባር እና ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት፤እና

(2) መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት በሚያከናውኗቸው ተጎጂዎችን የማዳን፣ የመመለስ፣መልሶ የማቋቋም እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች ላይ፤

4. <u>ዓላማ</u>

የፍልሰት ተጎጅዎችን ማዳን፣ መመለስ፣መልሶ ማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት፣ ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት ሁኔታ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የተቋማትን ሚና በመለየት እና ውጤታማ የቅብብሎሽ ሥርዓት በመዘርጋት፤ ወጥ፣ ተገማች፣ ተደራሽ እና ፍትሐዊ የሆነ የፍልሰት ተጎጅዎች ድጋፍና ጥበቃ እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡

5. <u>ጠቅላላ መርሆዎች</u>

ተጎጅዎችን የማዳን፣ የመመለስ፣ ከህብረተሰቡ ጋር የመቀላቀልና መልሶ የማቋቋም ድጋፎች የሚከተሉትን መርሆች፡-

(1) የተጎጂዎች ሙሉ ፈቃድ፣

(2) እኩልነት/ያለማዳላት፣

(3) የተጎጂዎችን የግል ፍላጎት ያማከለ መሆን፤

(4) የሴቶች፣ የህጻናት፣ የአዕምሮ ህመምተኞች እና የአካል ጉዳተኞችን ለአደጋ ተጋላጭነትና ልዩ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን፣

(5) ግላዊ ሚስጢራቸው እና ሰብዓዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ መሆን፣

(6) ፍትሀዊነት፣ አሳታፊነት እና ተጠያቂነት፣

(7) ቅልጥፍናና ውጤታማነት፡፡

## ክፍል ሁለት

### ስለ ብሄራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓቱ

6. **የቅብብሎሽ ሥርዓቱ ስለሚይዛቸው ጉዳዮች**

(1) ተጎጂዎችን ስለማዳን

(2) ተጎጂዎችን ስለመመለስ

(3) ተጎጂዎችን ከህብረተሰቡ ጋር ስለማቀላቀል

(4) ተጎጂዎችን መልሶ ስለማቋቋም

7. **የተቋማት የወል ተግባርና ሀላፊነት**

(1) በቅብብሎሽ ሂደቱ ዉስጥ አንድ ተቋም መስጠት ያለበትን አገልግሎት ለተጎጂው ሰጥቶ በተቋሙ የማይሸፈኑ አገልገሎቶችን በተመለከተየተጎጂውን መረጃ፣ የሰራውን ሥራ እንዲሁም የተገኙ ውጤቶችን በመመዝገብ አገልግሎቱንከሚሰጥ አግባብነትካለው አገልግሎት ሰጪ ተቋም ጋር ያገናኘዋል፡፡

(2) መረጃ የመለዋወጥና ተባብሮ የመስራት ሃላፊነት አለባቸው

(3) የቅብብሎሽ ስርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የዓሰራር ሥርዓቶችን ሊዘረጉ ይችላሉ፡፤

(4) በተጎጂዎች ላይ ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ ነገሮች ካሉ ለሚመለከተው የፍትህ አካል ያሳውቃሉ፡፡

8. **የተቋማት የተናጠል ተግባርና ሀላፊነት**

1) **የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

(1) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በውጪ ሀገር የሚገኙ የተጎጂ ኢትዮጵያውያንን መረጃ፣ የሚገኙበትን አገር፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃ በማጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፤

(2) ተጎጂው ውጭ ሀገር ታስሮ ወይም ተይዞ የሚገኝ ከሆነ ባለበት አገር የሚገኝ ወይም በቅርበት የሚሰራ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂው እንዲለቀቅ ጥረት ያደርጋል፡፡

(3) የተጎጂዎችን የድንገተኛ ጊዜ ድጋፍ ፍላጎት በመለየት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ ያደርጋል፤

(4) የጉዞ ሰነድ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ተጎጂዎች በራሳቸው ፈቃድ ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ በማድረግ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስረክባል፤

(5) በተጎጂዎች ላይ ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ መረጃዎች ካሉ ለሚመለከተው የፍትህአካልያሳውቃል፡፡

2) <u>**የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ**</u>

(1) ተጎጂዎችን በመመለስ ሂደት ውስጥ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የይለፍ ሰነድ እንዲያገኙ ያደርጋል።

(2) ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ ሃገር ተጎጂዎችን የመለየትና የመመዝገብ ስራ ይሰራል፤

(3) ከሚመለከታችው ሃገራት ሚሲዮንና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የውጭ ሃገር ዜጋ የሆኑ ተጎጅዎች ወደ ሃገራቸው የሚመለሱበት ሁኔታ በህግ በተሰጠው ሀላፊነት መሰረት ያግዛል፤

(4) ከኢትዮጵያ መውጫና ወደ ኢትዮጵያ መግቢያ ተብለው በተለዩ የድንበር ኬላዎች ላይ ተጎጂዎችን የመለየትና የመመዝገብ ስራዎችን ያከናውናል፤ በመመለስ ሂደትም ከሚመለከታችው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤ መረጃውንም ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሰጣል፡፡

3) <u>**የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒሰቴርና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች**</u>

(1) ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በሀገር ውስጥ የሚገኙ ተጎጂዎችን፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃ ያጠናቅራሉ፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳሉ፤

(2) በሀገር ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም ከወጪ አገር የተመለሱ ተጎጂዎችንየድንገተኛ ጊዜ ድጋፍ ፍላጎት በመለየት አግባብነት ካላቸው መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤

(3) የተጎጂዎችን ጠቅላላ የፍላጎት ጥናት በማድረግማህበራዊናየስነልቦናምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፤ በተቋሙ የማይሸፈኑአገልግሎቶችን በተመለከተአገልግሎቶቹን ወደሚሰጡ ተቋማት ይልካሉ፤

(4) በሀገር ውስጥ ወደ አካባቢያቸው መመለስ የሚፈልጉ ተጎጂዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ወደአካባቢያቸው እንዲመለሱ ያደርጋሉ፡፡

4) <u>ፖሊስ</u>

(1) ድንበር ሊያቋርጡ ሲሉየተገኙ ተጎጂዎችንለድጋፍ ሰጪ ተቋማት ይልካል፤ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ መረጃዎች ካሉ ምርመራ ያደርጋል፤

(2) በወንጀል በምርመራ እና በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት የተጎጂዎችን ደኅንነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ያደርጋል፤ ተጎጂዎች ሰብዓዊ በሆነ መንገድ የመያዝ መብታቸውን እንዲሁም ስለ ምርመራ ሂደቱ መረጃ የማግኘት መብታቸውን ያረጋግጣል፤

(3) በወንጀል በምርመራ እና በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ተጎጂዎች በማናቸውም ሁኔታ በፖሊስ ጣቢያ፣ በማረፊያ ቤት ወይም በማረሚያ ቤት እንዳይቆዩ ክትትል ያደርጋል፣ ይህ ሆኖ ሲገኝየማስተካከያ እርምጃእንዲወስድ ያደርጋል፤

(4) ምስክር ወይም ጠቋሚ በመሆኑ ምክንያት የተጎጂው ወይም የቤተሰቡ ህይወት ወይም ንብረት ለአደጋ የተጋለጠ እንደሆነ በምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 መሰረት ተገቢ ጥበቃ የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

(5) ተጎጂዎችቃለ-መጠይቅ ከማድረጋቸው በፊት ቃለ መጠይቁን ለመስጠት ፈቃደኛና ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ ቅድሚያ የስነ-ልቦና ወይም ሌላ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ይሄን ይፈጽማል፣ቃለ-መጠይቅ የሚደረግበት ቦታና ሁኔታምቹ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለተጎጂው ስለመብቶቹ እና ግዴታዎቹ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ አስፈላጊ ከሆነአስተርጓሚይመድባል፤

(6) የተጎጂውን ሁኔታና ፍላጎት ከግምት በማስገባት የተሻለ ድጋፍ እና እንክብካቤ ወደሚያገኝበት ተቋማት ይልካል፤

5) <u>**የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች**</u>

(1) ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተጎጂዎችንአስቸኳይየአደጋ እና ፍላጎት ጥናት ያከናውናሉ፤

(2) ህፃናት የሆኑ ተጎጂዎችን መረጃ በመሰብሰብ ተገቢውን የፍላጎት ልየታናዳሰሳ ያካሂዳሉ፤

(3) የድንገተኛ ጊዜ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተጎጂ ህፃናት ድጋፍ ይሰጣሉ፤

(4) ተጎጂ ህጻናት የማህበራዊ፣ስነ-ልቦና ድጋፍና ምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፣ከቤተሰብ የተነጠሉ ወይም ከማንም ጋር ያልሆኑ ተጎጂ ህጻናትን ቤተሰብ የማፈላለግና የማገናኘት ተግባር ያከናውናሉ፤ ይህን መፈጸም ካልተቻለ ሌሎች አማራጮችን ያመቻቻሉ፤

(5) በተቋሙ የማይሸፈኑ አገልግሎቶችን በተመለከተ አገልግሎቶቹን ወደሚያገኙበት ተቋም ይልካሉ፤

(6) በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጡ ድጋፎች የሴቶችና ህጻናትን ልዩ ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ መሆናቸውን ይከታተላሉ፡፡

6) <u>**ጤና ሚኒስቴርና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች**</u>

(1) የጤና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ተጎጂዎችይለያሉ።

(2) ተጎጂዎች የሚያስፈልጋቸውን የጤና አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡

(3) የስነልቦና ምክር እና የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ተጎጂዎች አስፈላጊውን አገልግሎትይሰጣሉ ወይም አገልግሎቱን ለሚሰጡ ባለድርሻ አካላት ይልካሉ፡፡

7) <u>**የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች**</u>

(1) የማህበረሰብ ጤና ስጋት ካሉባቸው ሀገራት የሚመለሱ ተጎጂዎችን በተመለከተ ቀድሞ መረጃ በማሰባሰብ በቂ ዝግጅት ያደርጋሉ፤

(2) ተጎጂዎች በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች የማህበረሰብ ጤና ስጋት ወይም ወረርሽኝ እንዳይከሰት የመከላከል ስራ ይሰራል፤ በሽታው ከተከሰተም ስርጭቱን ለመግታትና ተጎጂዎችን ለመታደግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፤

(3) የማህበረሰብ ጤና ስጋት ወይም ወረርሽኝ በሚከሰትበት ወቅት በመግቢያ ኬላዎች ላይ የመለየት፣ የመመርመር እንዲሁም የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ፤

8) <u>**ጠቅላይ ዐቃቤ ህግና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች**</u>

(1) ተጎጂዎች ከምርመራ በፊት፣ በምርመራ ወቅት፣ በፍርድ ሂደትና ከፍርድ በኋላ ስላሏቸው ዝርዝር መብቶች እና ግዴታዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

(2) ተጎጂዎች ሰብአዊ መብቶቻቸው መከበሩን ያረጋግጣሉ፤ በፖሊስ ጣቢያ፣ በማረፊያ ቤት ወይም በማረሚያ ቤት አለመቆየታቸውን ይከታተሉ፤ መብቶቻቸው ተጥሶ ሲገኝ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፡፡

(3) የፍርድ ቤት ችሎት አደረጃጀትና የክርክር ሂደት ለተጎጂ ምስክሮች ምቹ መሆኑን ያረጋግጣሉ፤

(4) ለተጎጂ ምስክሮች በምስክሮች ጥበቃ አዋጅ 699/2003 መሰረት ከለላ ያደርጋሉ፡፡

(5) ጊዜያዊ የመጠለያ፣ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የህክምና፣ የስነልቦናና የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ተጎጂዎች አገልግሎትን ወደሚያገኙበት ተቋም ይልካሉ፣

(6) ተጎጂዎች ጋር በመመካከር ለወንጀል ችሎቱ በማመልከት የካሳ ውሳኔ በማስወሰን ተከታትሎ ያስፈጽማሉ፤

(7) የተጎጂዎችን የፍትሀብሄር ጉዳዮች በተመለከተ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/08 አንቀጽ 6(4) ወይም በክልሎች ተመሳሳይ ህጎች መሰረት ይፈፅማሉ፡፡

9) **<u>የፌዴራል ከተሞች ሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች</u>**

(1) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተጎጂዎች ይለያሉ፤ ያደራጃሉ፤ መልሶ የማቋቋም ሥራ ይሰራሉ፤

(2) በመልሶ ማቋቋም ሥራ ተጠቃሚዎች የልየታ፣ ምዝገባ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የመስሪያና ቦታ አቅርቦት እንዲሁም አስፈላጊውን የገበያ ትስስር ድጋፍ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፣

(3) ተጎጂዎችበየሥራ መስካቸው የሚኖርባቸውን የንግድ ስራ አመራር እና የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተት አጥንቶ የሥራ ፈጠራና የንግድ ሥራ አመራር ስልጠናዎችን ይሰጣል፤ የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻሉ፣

(4) በየስራ መስካቸው የሚያስፈልጋቸውን የብድር አገልግሎት በመለየት ከአነስተኛ አበዳሪ ተቋማት የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻሉ፣

(5) ዘመናዊ የንግድ ሥራ አመራርና የአሰራር ስርዓት፣ የሂሳብ አያያዝና የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፣

(6) እንደየአካባቢው ተጭባጭ ሁኔታ አዋጭ የንግድ ሥራ ዳሰሳ ጥናት ያደርጋል፤ ሞዴል የንግድ ሥራ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤

(7) በተቋሙ የማይሸፈኑ አገልገሎቶችን በተመለከተ አገለግሎቱን ለሚሰጡ ተቋማት ይልካሉ፡፡

10) **<u>የገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሰሩ በየደረጃው ያሉ ተቋማት</u>**

(1) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተጎጂዎች ይለያሉ፤ ያደራጃሉ፤ በተለያዩ የግብርና፣ የማዕድን ማውጣትና ሌሎች የገጠር የሥራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ የመልሶ የማቋቋም ሥራ ይሰራሉ፤

(2) በመልሶ ማቋቋም ሥራ የተጎጂዎች ልየታ፣ ምዝገባ፣ የስራ ዕድል ፈጠራ እና የመስሪያና ቦታ አቅርቦት እንዲሁም አስፈላጊውን የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ድጋፍ ያደርጋሉ፤

(3) ተጎጂዎች በየተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚኖርባቸውን የስራ አመራር እና የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተቶችን አጥንቶ የሥራ አመራር ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፤ የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻሉ፣

(4) በየስራ መስካቸው የሚያስፈልጋቸውን የብድር አገልግሎት በመለየት ከአነስተኛ አበዳሪ ተቋማት ብድር የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻሉ፣

11)<u>**የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች**</u>

(1) የተጎጂዎችን ልዩ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ያዘጋጃሉ፣

(2) ተጎጂዎችን ወደ ሥራ ሊያስገባ የሚያስችል አጫጭርየግንዛቤ፣ የስራ አመራርና የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና ይሰጣሉ፣

(3) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተጎጂዎችበመለየት አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

12)<u>**አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶች**</u>

(1) የተጎጂዎችን የብድር ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል የአሰራር ዘዴ ይቀይሳሉ፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅተው ተግባራዊ ያደርጋሉ፣

(2) ለተጎጂዎች በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የቁጠባ፣ የብድር ስርጭትና አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣሉ፡፡

(3) ለተጎጂዎች የሚያስፈልግ የፋይናንስ አቅርቦትን ያመቻቻሉ፣

(4) ለተጎጂዎች የተሰራጨ ብድር ለታሰበለት ዓላማ ስለመዋሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፤

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የድጋፍ ክትትል ስርዓት</u>

9. <u>የድጋፍና ክትትል ስርዓት</u>

1. ብሄራዊ ምክር ቤቱበዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ ላይ የተመለከቱትን ተግባራት ይፈፅማል።
2. ለብሄራዊ ምክር ቤቱ ተጠሪ የሆነው የትብብር ጥምረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦
   I. ይህ መመሪያ በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣ ለዚህምየተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
   II. በየደረጃው ካሉ አካላት በየሩብ አመቱ ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል፣
   III. በቅብብሎሽ ስርዓቱ በፌዴራልና በክልሎችመካከል የሚኖረውን የቅንጅትና ትብብር ስርዓትን ይደግፋል፣ያጠናክራል፣
   IV. በዓመት ሁለት ጊዜ የግምገማ መድረክ ይዘጋጃል፣
   V. ከሁሉም የቅብብሎሽ ስርዓቱ ከሚካሄድባቸው ቦታዎች ናሙና በመውሰድ የዳሰሳ ጥናት ያደርጋል፣
   VI. በመመሪያው አፈጻጸም የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፣ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
   VII. በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሰረት ያከናወናቸውን ተግባራት ለብሄራዊ ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. የክልል የፍልሰት ትብብር ጥምረቶች ይሄንን መመሪያ መሰረት በማድረግ እንደየክልላቸው ነባራዊ ሁኔታ የቅብብሎሽ ስርዓት መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

10.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም አካል ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

11.<u>የህግ ተጠያቂነት</u>

በዚህ መመሪያ ሀላፊነት የተሰጣቸው አካላት ሃላፊነታቸውን ካልተወጡ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

12.<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

የፍልሰት ብሔራዊ ምክር ቤትይህ መመሪያ ሊሻሻል ይገባዋል ብሎ ሲያምን የማሻሻል ስልጣን አለው፡፡

13.<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ---ወር--ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡